ኢብራሒም ዓለይሂ-ሠላም

t.me/
tafachdaewachanal

#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
@tafachdaewachanal
#ክፍል (አንድ)
ቁርአን እንድህ ይላል፦ ﴿
وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ إِبۡرَٰهِيمَۚ إِنَّهُۥ كَانَ صِدِّيقٗا نَّبِيًّا
በመጽሐፉ ውስጥ ኢብራሂምንም አውሳ። እርሱ በጣም እውነተኛ ነቢይ ነበርና። (አል መርየም 41)
#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የነብያቶች አባት በመባል ይታወቃል ይህም የሆነው አብዘሀኞቹ ነብያቶች ከ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ዘር የወጡ በመሆናቸው ነው። #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ለተውሂድ ከፍተኛ ተጋድሎ ካደረጉት ድንቅ ነብያቶች መካከል ናቸው።
#ኸሊሉሏህ (የ አላህ ልዩ ወዳጅ) በመባልም ይታወቃሉ።
ወደ ታሪካቸው ስንገባ፦ #ኢብራሒም በ አንዳንድ ዘገባወች መሰረት ወላጅ አባታቸው ታሩኽ ይባል እንደነበርና ቅን የሆነ አማኝ ሰው እንደነበር ይነገራል። ታሩኽ ሞተና የ #ኢብራሒም እናት #አዘርን አገባች። አዘር የ #ታሩኽ ወንድም ነበር። በዚህ ምክናየት ጣኦት አምላኪው አዘር የ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አባት ሆነ። በሌላ ዘገባ መሰረት ደግሞ ታሩኽ የሚለው ስም የኢብራሒ (ዐለይሂ ሰላም) አባት የቀድሞ ስም ሲሆን ጣዖት ማምለክ ሲጀምር ስሙ በሚያመልከው ጣኦት ተቀይሮ አዘር ተባለ።
ቁርአን ﴿
وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ ءَازَرَ أَتَتَّخِذُ أَصۡنَامًا ءَالِهَةً ۖ
#ኢብራሒምም ለአባቱ ለአዘር «ጣዖታትን አማልክት አድርገህ ትይዛለህን?
(አል አንዐም 74)
ይህ የቁርአን አያ ሁለት ሀሳቦችን ያሳየናል አንዱ በቀጥታ የ ኢብራሒም አባት ስም አዘር እንደሆነ ሁለተኛው ኢብራሒም ለ አባቱ አዘር የሚባለውን ጣኦት አምላክ አድርገህ ትይዛለህን? ለማንኛውም የኢብራሒም አባት አዘርም ሆነ ታሩኽ ሁለቱንም ሀሳብ በ አንድ አጣምሮ የሚዝልን ነገር ቢኖር አባታቸው ጣኦት አምላኪ መሆኑ ነው ይህም የተከበረው ቁርአን ﴿ ያስረዳናል፦
#ኢብራሒም ለአባቱ ባለ ጊዜ (አስታውስ) «አባቴ ሆይ! የማይሰማንና የማያይን ከአንተም ምንንም የማይጠቅምህን (ጣዖት) ለምን ትግገዛለህ? (መርየም 42)
ስለ አባቱ ይህን ካልን ወደ ውልደቱ እና እድገቱ እናምራ፦
በኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ዘመን እንደ ፊርአውን

ጌትነትን ለራሱ ያደረገ ሰው ነበር። ስሙ (ኑምሩዝ) ይባላል። ኑምሩዝ በጣም ሀብታምና ባለ ስልጣን ነበር። ይህንንም ቁርአን ፩ እንድህ ሲል ያወሳዋል፦

#ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው ሰው አላየህምን (አል በቀራህ 258)

ይህ ሰው ኢብራሒምን የተከራከረበትን ጉዳይ በቀጣይወቹ ክፍሎች ምናየው ይሆናል። ኑምሩዝ አንድ ለሊት ላይ ህልም እንዳየ ይነገራል፦ ይህም ህልም ሰማይ ላይ የሚያብረቀርቅ ብርሀን የመጣ ይመስለዋል። ይህ ብርሀን የፀሀይን እና የጨረቃን ብርሀን አጠፋ። በሌላ ዘገባ ደግሞ አንድ ሰው ወደ ዙፋኑ መጥቶ ከ ዙፋኑ ሲያወርደው እና በ ሀይል መሬት ላይ ሲጠለው ነበር የተመለከተው ተብሏል። ከ እንቅልፉ ሲነቃ በጥልቅ ፍርሀት ውስጥ ተዋጠ። ኮከብ ቆጣሪወችን ወደ ቤተ መንግስቱ አስጠራ። ያየውን ሁሉ ነገራቸው። እነርሱም እንድህ አሉት፦

#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ......#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)

#ክፍል (ሁለት)

ኑምሩዝ ያየው ህልም ስላስጨነቀው ፍቹን ለማወቅ በመጓጓት በሀገሪቱ የታወቁ የሆኑ ኮከብ ቆጣሪወችን አስመጥቶ ያየውን ህልፍ ፍች እንዲነገሩት ጠየቃቸው። እነርሱም እንድህ አሉት፦ አድስ ሀይማኖት ሊመጣ ነው። ይህንን ሀይማኖት ይዞት ሚመጣው ሰው ዙፋንህን ያጠፋዋል። ነገሩን አስብበት ለዚያች ቀን ተዘጋጅ ሲሉ ቆንጆ መርዶ አረዱት።

በዚህ መሰረት ኑምሩዝ እና አማካሪው ውሳኔን አስተላለፉ። ውሳኔው ከዛን ቀን ጀምሮ ሚወለዱ ልጆችን መግደል በዚህም የተነሳ እስከ መቶ ሺ ህፃናት እንደገደለ ይነገራል። ይሄ ብቻም አልበቃ ብሎት ጭራሽ ወንዶች ሚስቶቻቸውን እንዳይገናኙ ጥብቅ ትዛዝ አስተላለፈ። ባል እና ሚስቶችን የተለያየ ቦታ አስደርጎ በወታደር ማስጠበቅ ጀመረ። የ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አባት የ ኑምሩዝ ቅርብ ባለ ሟል ነበር እና በ አንድ ለሊት ኑምሩዝ አዘርን የሆነ ነገር እንዲያመጣ ወደ ቤቱ ይልከዋል በዚህን ጊዜ ሚስቱን ይገናኛትና ኢብራሒምን ታረግዛለች። ተደብቃ ኑራም እርግዝናዋን በጨረሰች ጊዜ ከባቢሎን በስተ ምስራቅ በኩል ደጀላ እና ፋራት በመባል በሚታወቁ ወንዞች መካከል በሚገኝ አከባቢ ተወለዱ።

ከዛም ሸለቆ ውስጥ አውሬ እንዳይበላው መጠለያ ሰሩለት። እናታቸውም ከሰወች እይታ በመራቅ ወደ ዋንሻው በመሄድ ታጠባቸው ነበር። ልታጠባቸው በሄደችበት ሰአትም ለየት ያለን ነገር ታይ ነበር እርሱም ህፃን ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ጣቶቹን ሲጠባ ወተት እና የማር ጭማቂ እንድሁም ውሃ እየፈለቀለት ከዛ ይመገብ ነበር።
ህፃን ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በዚህ ዋንሻ ውስጥ እድገታቸው በጣም ይፈጥን ነበር በተወለዱ በ አንድ አመታቸው የሶስት አመት ልጅ አከሉ። ኑምሩዝ ደግሞ በዚህ አመት ውስጥ የተወለደ ልጅ ነው ስልጣንህን ያጠፋዋል የተባለው ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በዘንድሮ አመት የተወለዱ አይመስሉም ስለዚህ ወታደር ቢያቸውም ግድያው እሳቸውን አይመለከታቸውም ነበር ከዚያም አመታት ተቆጥረው ትንሽ ከፍ ባሉ ጊዜ እናታቸውን እንግዳ የሆነባትን ጥያቄ ጠየቋት ማነው ጌታየ? አሏት እርሷም እኔ አለችው። ያንችስ ጌታ ማነው? አላት አዘር አለችው። የ አዘርስ ጌታ ማነው? ሲል ጥያቄውን ቀጠለ እናቱም የ አዘር ጌታ ኑምሩዝ ነው አለችው። ኢብራሂም (ዐለይሂ ሰላም) ነገሩን ችላ ማለት አልፈለገም ነበር እና የ ኑምሩዝ ጌታስ ማነው? አላት በዚህን ጊዜ የታየው ህልም እና ያጠፋሀል የተባለው ሰው ይሄ ነው ማለት ነው ብላ በድንጋጤ ተሞልታ ዝም በል ብላ ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) በጥፊ መታችው ነገሩን በዛው የምትቋጭ መስሏት።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

http://t.me/AshaBuleyamine
#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል (ሶስት)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የጣኦቶቹ መመለክ ገና ከልጅነታቸው ነበር ራስ ምታት የሆነባቸው ። ይህ ሳያንሳቸው አባታቸው ዋና የጠኦት ተገዥና ቀራጭ ነበር እንድሁም የእጁ ስራ ውጤቶች የሆኑትን አምላክ እያለ ሚሞግታቸውን ቅርፃቅርፅ ወደ ገበያ በማውጣት ይሸጣል። ኢብራሒምንም እንዲሸጡ ያዛቸው ነበር። ኢብራሂም (ዐለይሂ ሰላም) ግን ምንም እንኳ ገና ለጋ ወጣት ቢሆኑም ጣኦቶቹ ምንም የማይጠቅሙና የማይጎዱ መሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃል እንድሁም ይጠላቸዋል። እንዲሸጥ የተላከውንም ጣኦት በገመድ አስሮ እየጎተተ

ይወስደዋል ከዛም ውሃ እላውላይ በማፍስስ ውይ ውይ ውሃ ጠምቶታል እያለ ይሳለቅበትና ያሾፍበት ነበር።
ከዚያም ደግሞ የማይጠቅም ግን ሚጎዳችሁን ሚገዛ እያለ በጣኦቱ ያሾፍ እና ይሳለቅበት ነበር። እናም ሌሎቹ ጣኦት ሻጭወች ሸጠውና አትርፈው ሲመለሱ ኢብራሂም (ዐለይሂ ሰላም) ግን እንደነበረ አልሸጥ አለኝ በማለት ለ አባታቸው ይመልሱለታል።
ይህ ማለት ግን ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ጣኦት ይሸጥ ነበር ማለት አይደለም ይልቁንም በጣኦቱ ሲሳለቅና የማይጠቅም የሚጎዳ ሚገዛ እያለ ሲያስተዋውቅ ሰወች ራሳቸውን እንዲጠይቁ ለማድረግ ነው። እንጅ ኢብራሂም ጣኦትን አይሸጥም ምክናየቱም አላህ ለ ኢብራሂም (ዐለይሂ ሰላም) ገና በልጅነታቸው ነበር ደግና ክፉውን እንዲለዩ እንድሁም ቀጥተኛውን መንገድ እንዲይዙ የመራቸው። ቁርአን ፅ
#ለኢብራሂምም ከዚያ በፊት ቅን መንገዱን በእርግጥ ሰጠነው። እኛም በእርሱ (ተገቢነት) ዐዋቂዎች ነበርን።
(አል አንቢያዕ 51)
ሲቀጥል ኢብራሂም በልጅነቱ ጀምሮ የ አይሁድ ወይም የክርስቲያን እምነት ተከታይ እንዳልሆነ እንድሁም በ አላህ ላይ አሻራኪ እንዳልነበረ አላህ በቁርአን እንድህ ሲል ይናገራል ቁርአን ፅ
مَا كَانَ إِبۡرَٰهِيمُ يَهُودِيّٗا وَلَا نَصۡرَانِيّٗا وَلَٰكِن كَانَ حَنِيفٗا مُّسۡلِمٗا وَمَا كَانَ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ
#ኢብራሂም ይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም። ግን ወደ ቀጥተኛው ሃይማኖት የተዘነበለ ሙስሊም ነበረ።
ከአጋሪዎችም አልነበረም። (አል ኢምራን 67)
ኢብራሂም (ዐለይሂ ሰላም) ነብስ ካወቀበት ጀምሮ አላህ የመራውና ቀጥተኛ መንገድ ላይ ያለ ታላቅ ነብይ ነው።
በዚህም ምክናየት የተሰጣቸውን ተፈጥሯዊ የአዕምሯዊ ብስለት ተጠቅመው ሰወችን ወደ ተውሂድ ጋበዙ።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ....
http://t.me/AshaBuleyamine
#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል (አራት)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ገና በለጋ እድሚያቸው ትኩረታቸውን #ተውሂድ ላይ በማድረግ የዳዕዋ ጥሪያቸውን በተወለዱባት ሀገር ጀመሩ።
አላህም (ሱብሀኑ ተዐላ) ለኢብራሂም እንዲያውቅና ከ

አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ውጭ ያሉ ማንኛቸውም ነገሮች ሊመለኩ እንደማይገባ የሰማያት እና የምድርን መለኮቶችን አሳየው። ቁርአን ፩
#እንደዚሁም ኢብራሂምን (እንዲያውቅና) ከአረጋጋጮቹም ይኾን ዘንድ የሰማያትንና የምድርን መለኮት አሳየነው። (አል አንዐም 75)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በልጅ አዕምሮው እነሱ ሚያመልኳቸው አምላኮች ስላልተመቸው እና ምንም እንደማይጠቅሙ ስለገባው ከእነሱ ጣኦቶች ወደተሻለ ነገር ተመለከተ። እናም ለሊቱ በጨለመ ጊዜ ሰማይ ላይ ከዋከብትን ተመለከተ። በዚህን ጊዜ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ከዋከብቶቹ አባቱን ጨምሮ ከሚያመልኳቸው ድንጋይዎች ተሸለው ስላገኛቸው በቃ ይሄ ጌታየ ነው ሲል አሰበ ግን ከቆይታ በኋላ ኮከቦቹ ጠለቁ በዚህን ጊዜ ከገባማ እንዴት ጌታ ሊሆነኝ ይችላል አይ ይሄን በጌትነት መያዝ አልፈልግም አለ። ቁርአን ፩
#ሌሊቱም በእርሱ ላይ ባጨለመ ጊዜ ኮከብን አየ። «ይህ ጌታዬ ነው» አለ። በጠለቀም ጊዜ፦ «ጠላቂዎችን አልወድም» አለ። (አል አንዐም 76)
በዚህን ጊዜ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሌላን ከሱ ከኮከቡ የተሻለን ፈለገ እናም ጨረቃን አብሪ ሁኖ ተመለከተው ከዛም ይህ ነው ጌታየ ሲል አሰበ ጨረቃውም ለፀሀይ ቦታውን ለቆ በገባ ጊዜ ይሄም ለጌትነት ብቁ እንዳልሆነ አመነ። አላህም ቅኑን መንገድ ባይመራኝ ኑሮ እኔም እንደ አባቴ እና መሰሎቹ የተሳሳትኩ እሆን ነበር አለ። ቁርአን ፩
#ጨረቃንም ወጪ ኾኖ ባየ ጊዜ፦ «ይህ ጌታዬ ነው» አለ። በገባም ጊዜ፦ «ጌታዬ (ቅኑን መንገድ) ባይመራኝ በእርግጥ ከተሳሳቱት ሕዝቦች እኾናለሁ» አለ። (አል አንዐም 77)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በዚህ አላበቃም ከሁሉም ደምቃ የምትታየውን እና ጨለማን ገፋ ብርሀን የምትሞላውን ፀሐይን ጮሬዋን ዘርግታ ተመለከታት። በቃ አሁን ከሁሉም የተሻለ የሆነ አምላክ አገኘሁ ሲል አሰበ ነገር ግን ፀሐይም እንደሌሎቹ ብርሀኗን ለጨለማው ለቃ ተሰወረች በዚህን ጊዜ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) እንኳን የእነሱ ደካማ ፍጡር ድንጋይ ጠርቦ የሰራቸው ጣኦት ቀርቶ ታላላቆቹ ፀሐይ፣ጨረቃ፣ከዋከብት እንኳ ለ አምላክነት የማይበቁ መሆናቸውን ተረዳ። ህዝቦቹንም እኔ

ከምታጋሩት ነገር ሁሉ የጠራሁ ነኝ ሲል ራሱን ግልፅ አደረገላቸው። ቁርአን ፩
#ፀሐይንም ጨራዋን ዘርግታ ባየ ጊዜ፦ «ይህ ጌታዬ ነው። ይህ በጣም ትልቅ ነው» አለ። በገባችም ጊዜ፦ «ወገኖቼ ሆይ! እኔ ከምታጋሩት ሁሉ ንጹሕ ነኝ» አለ።
(አል አንዐም 78)
ፊቱንም ወደ ብቸኛውና ሀያሉ አምላክ የሰማይ እና የምድ በመካከላቸውም በውስጣቸውም ያለው ነገር ሁሉ ፈጣሪ ወደሆነው #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) እንዳደረገ በግልፅ ነገራቸው። ቁርአን፦ ፩
#«እኔ ለዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው (አምላክ) ቀጥተኛ ስኾን ፊቴን አዞርኩ። እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም» (አለ)። (አል አንዐም 79)
በዚህን ጊዜ ህዝቦቹ ይከራከሩት ያዙ፦
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ...

https://t.me/joinchat/AAAAAEV2Kb4hUy-9DkHbtg
#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል (አምስት)

ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የሰማይ እና የምድር መለኮቶች ከተገለጡለት በኋላ ከ አላህ ውጭ የሚያመልኳቸውን አማልክት በግልፅ ማስተባበል ጀመረ። በዚያውም የመጀመሪያ የተውሂድ ጥሪውን ከ አባቱ ጀመረ። አለው አባቴ ሆይ፦ ኢብራሒም ለ ሙሽሪኩ አባቱ ልስላሴ በተሞላበት አንደበት አባትነቱን እንዳከበረ አባቴ ሆይ! ሲል በመልካም ቃል ጥሪውን ጀመረለት። የተውሂዱን ጥሪ በጥያቄ ነበር የጀመረው፦ ቁርአን ፩
#ለአባቱ ባለ ጊዜ (አስታውስ) «አባቴ ሆይ! የማይሰማንና የማያይን ከአንተም ምንንም የማይጠቅምህን (ጣዖት) ለምን ትግገዛለህ? (መርየም 42)
በመጀሪያ መስማትም ማየትም የተሳናቸው መሆኑን ነገረው ሲቀጥል ምንም ሊጠቅሙት እንደማይችሉ አስገነዘበው ከዚያም እነዚህን ምንም ጥቅም የለላቸውን ነገሮች ለምን እንደሚገዛቸው በመገዛቱ ምን ሊያገኝ እንደሚችል በጥያቄ መልኩ አሳሰበው።
#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ንግግሩን ቀጠለ፦ ቁርአን ፩
#«አባቴ ሆይ! እኔ ከዕውቀት ያልመጣልህ ነገር በእርግጥ መጥቶልኛልና ተከተለኝ። ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና።

(መርየም 43)
ኢብራሒም ጥቅም አልባ ነገር መገዛቱ ምንም
እንደማይጠቅመው ከነገረው በኋላ ወደ መፍትሄው
መጣለት። መፍትሄው እኔን መከተል ነው አለው።
ምክናየቱም ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የሱ ልጅ
ቢሆንም ለእርሱ ያልመጣለት እውቀት መቶለታል አላህ ከሱ
ውጭ ያሉ አማልክትን እንዳያመልክ ቀድሞ አሳውቆታል
ስለዚህ አዘር ያለው አማራጭ መዳን ከፈለገ ኢብራሒምን
መከተል ብቻ ነበር።
ግን ፍቃደኛ አልሆነም በእንቢተኝነቱ ፀና። እንቢተኝነቱ
ሀቅን ከመቀበል ጋረደው ለዚህም ዋነኛ ምክናየት ሸይጧን
እንደሆነ ግልፅ ነውና እሱን ከመታዘዝ እንዲቆጠብ
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አሳሰቡት። ቁርአን፡- ፆ ፣
#«አባቴ ሆይ! ሰይጣንን አትግገዛ። ሰይጣን ለአልረሕማን
አመጸኛ ነውና። (መርየም 44)
ሰይጣን ለጌታው አመፀኛ ነው። እናም እርሱን ከተከተልክ
የሱ ጓደኛ ነው የምቶነው እሱ ደግሞ መጨረሻው ጀሀነም
ነው። ስለዚህ ከዚህ ድርጊትህ ተቆጥበህ ኢስላምን
ልትቀበል ይገባል። ያ ካልሆነ ግን ወደፊት ከሚገጥምህ የ
አላህ ቅጣት እኔ እፈራልሀለሁ እባክህ አባቴ ሆይ ሲል
በትህትና እየደጋገመ አስረዳው። ቁርአን፡- ፆ
#«አባቴ ሆይ! እኔ ከአልረሕማን ቅጣት ሊያገኝህ
ለሰይጣንም ጓደኛ ልትኾን እፈራለሁ።» (መርየም 45)
የ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አባት ግን ይሄን ትህትና
የተሞላበት የልጁን ምክር በደስታ ከመቀበል ይልቅ በቁጣ
እና በንዴት ተሞልቶ ኢብራሂምን እንድህ ሲል ተናገራቸው፡-
ቁርአን ፆ
#(አባቱም) «ኢብራሂም ሆይ! አንተ አምላኮቼን ትተህ
የምትዞር ነህን ባትከለከል በእርግጥ እወግርሃለሁ። ረዥም
ጊዜንም ተወኝ» አለ። (መርየም 46)
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ...

https://t.me/joinchat/
AAAAAEV2Kb4hUy-9DkHbtg
@tafachdaewachanal
#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል (ስድስት)
አዘር የ ልጁን ታላቅ ምክር እና ግሳፄ ሰምቶ ወደ አላህ
እንደመመለስ ጭራሽ ምንም ለማይጠቅሙት በጁ ጠራርቦ

ለሰራቸው ድንጋይወች ተቆርቁሮ አምላኮቸን ትተህ ሌላን አምላክ ይዘህ ልታወግዛቸው ትፈልጋለህ ከዚህ ድርጊትህ ልትቆረቆር ይገባል ካልሆነ ግን እመተሀለሁ እንደውም አይኔ ወድማያይብህ ቦታ ሂድ ከኔ ራቅ ሲል ቁጣ ያዘለ ዛቻውን ዛተባቸው።።
ኢብራሒምም (ዐለይሂ ሰላም) ንግግራቸውን በመልካም አንደበት እንደጀመሩ በመልካም አጨራረስ ተሰናበቱት ቁርአን፡- ፭
#«ደህና ኹን። ወደፊት ከጌታዬ ምሕረትን እለምንልሃለሁ። እርሱ ለኔ በጣም ርኅሩኅ ነውና» አለ። (መርየም 47)
አባቴ ሆይ! ደህና ኹን ሚገርም መልስ ሰጡት አባትነት ክብሩን አላሳጡትም ከፍ ዝቅ አድርገው አላናገሩትም እንደውም አላህን ምህረት እለምንልሀለሁ ብለው በሰላም ተሰናበቱት።።
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አባታቸውን በዚህ መልክ ደዕዋ አድርገው ምላሹ ባያስደስታቸውም እንኳ ተስፋ ግን አልቆረጡም አባቴ ካልሰማኝ ማን ሊሰማኝ ብለው ከዳዕዋ አልተቆጠቡም። እንደውም ከመጀመሪያው ከፍ ባለ ደረጃ ዳዕዋቸውን ጀመሩ። አባታቸውንም ህዝቦቻቸውንም ሚያመልኩት አምላክ ምን እንደሁ ጠየቋቸው። ቁርአን፡- ፭
#ኢብራሒም ለአባቱና ለሕዝቦቹ «ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ ያቺ እናንተ ለእርሷ ተገዢዎች የኾናችሁት ምንድን ናት» ባለ ጊዜ (መራነው)። (አል አንቢያዕ 52)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አባቱ እና ህዝቦቹ ሚያመልኩትን አምላክ ምንነቱንና ማንነቱን እንዲያብራሩላቸው እድሉን ሰጧቸው ግን ስለ ምንነቱ እና ስለማንነቱ መልስ አልነበራቸውም። ምክናየቱም የማይጠቅም የማይጎዳ ከድንጋ እና ከእንጨት የተጠረበ ግዑዝ ነገር መሆኑ ሀገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ጉዳይ ስለሆነ። ብቻ መልስ መመለስ ስለነበረባቸው ተራ የሆነ መልስ መለሱላቸው፡- ቁርአን ፭
#«አባቶቻችንን ለእርሷ ተገዢዎች ኾነው አገኘን» አሉት።
(አል አንቢያዕ 53)
ይህ ነበር መልሳቸው የድንቁርና መልስ አባቶቻቸው ስለተገዟቸው ብቻ ይገዟቸዋል እንጅ ይፈጥራል ይገድላል ይጠቅማል ይጎዳል እነሱ ዘንድ አሳሳቢ አልነበረም ይህንንም በማድረጋቸው እነሱም አባቶቻቸውም የተሳሳቱ መሆናቸውን ኢብራሒም ነገሯቸው፡- ቁርአን
#«እናንተም አባቶቻችሁም በእርግጥ በግልጽ ስህተት

ውስጥ ነበራችሁ» አላቸው። (አል አንቢያዕ 54)
ስለዚህ ስህተት ላይ መሆናችሁን አምናችሁ ተመለሱ ነው።
ግን እነሱ መመለስን አይደለም በስህተት ውስጥ ናችሁ
ማለቱ አናዷቸው ምን ለማለት ፈልገህ ነው አይነት ንግግር
ተናገሩት፦ ቁርአን፩
#«በምሩ መጣህልን ወይንስ አንተ ከሚቀልዱት ነህ»
አሉት። (አል አንቢያዕ 55) እና እየቀለድክ ነው ወይስ
የምር ተሳስታችኋል እያልክ ነው ሚልን ቁጣ አዘል ጥያቄ
ሲያቀርቡለት ኢብራሒምም በበኩሉ እየቀለደ እንዳልሆነና
ጌታቸው የነሱ እንጨት እና ድንጋ ሳይሆን ታላቁ አላህ
(ሱብሀነሁ ተዐላ) መሆኑን በሚገባቸው ቋንቋ አስረዳቸው።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

https://t.me/joinchat/
AAAAAEV2Kb4hUy-9DkHbtg
#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል (ሰባት)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ህዝቦቹ እነሱም ሆኑ
አባቶቻቸው በተሳሳተ መንገድ ውስጥ እንዳሉ በሚነግራቸው
ጊዜ በቁጣ አንደበት የምርህን ነው ወይስ እየቀለድክ
ብለው በሱ ላይ ተነሱበት ኢብራሂም (ዐለሂ ሰላም)
እየቀለደ እንዳልሆነ እና አምላካቸው ሰማይና ምድርን
የፈጠረው አላህ እንደሆነ ባይፈልጉም ነገራቸው። ቁርአን፦
፩
#«አይደለም ጌታችሁ የሰማያትና የምድር ጌታ ያ
የፈጠራቸው ነው። እኔም በዚህ ላይ ከመስካሪዎቹ ነኝ»
አለ። (አል አንቢያዕ 56)
እነሱ የሚያመልኩት ጣኦት እነርሱ የሰሯቸው ሲሆኑ
ኢብራሒም የሚያመልከው አምላክ ደግሞ የሚኖሩበትን
ምድር እንድሁም ከላይ የጠለሉበትን ሰማይ የፈጠረ ከፍ
ያለ እና የተላቀ አምላክ መሆኑን አብራራላቸው። ሊሰሙት
ፍቃደኛ አይደሉም በዚህን ጊዜ ኢብራሒም ድምፁን
በመቀነስ እንድህ አላቸው፦ ቁርአን፩
#«በአላህም እምላለሁ ዟሪዎች ኾናችሁ ከሄዳችሁ በኋላ
ጣዖቶቻችሁን ተንኮል እሠራባቸዋለሁ» (አለ)። (አል
አንቢያዕ 57)
ይችን ንግግሩን ቀስ ብሎ ቢናገራትም አንዳንድ ሰወች
ሰምተውት ነበር። ሰወችም በ አመት አንዴ ሚሰባሰቡበት
ቦታ ነበራቸው እና ወደዛ ሲያመሩ ኢብራሂም ላሰበው ስራ

አመች ጊዜ እንደሆነ አወቀ። ሰወች ግን ና እንጂ አብረን እንሂድ አሉት በዚህን ጊዜ ያለበት መሀበረሰብ ኮከብ አምላኪ ስለሆኑ ወደ ኮከብ ተመለከተ ቁርአን፦ ፅ #በከዋክብትም መመልከትን ተመለከተ። (አ ሷፋት 88) ከዛም እንድህ አለ፦ ቁርአን ፅ #«እኔ በሽተኛ ነኝም» አለ። (አ ሷፋት 89) ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በሽተኛ ሁኖ ሳይሆን ህዝቦቹ ወደ ሚሰበሰቡበት ቦታ አብሮ ላለመሄድ የፈጠረው ሰበብ ነው ወደ ኮከብ ተመልክቶ እኔ በሽተኛ ነኝ ያለው ይህ ኮከብ በመውጣቱ ታምሚያለሁ እና እዚሁ ነው ምቀረው ነው ህዝቦቹም ኮከብ አምላኪ ስለሆኑ እነሱ የሚያደርጉት ልማዳቸው ስለሆነ አመኑት እና ሁሉም ወደ ሚሰበሰቡበት ቦታ ሄዱ።
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በሄዱለት ጊዜ ወደ አማልክቶቻቸው ሄደ ቁርአን ፅ #ወደ አማልክቶቻቸውም ተዘነበለ። (አ ሷፋት 91) እንዳለ ተደርድረው ከፊት ለፊታቸው ምግብ ቀርቦላቸው አኖ` ለድንጋይ ምግብ ቀርቦ ኢብራሒም በመገረም እንድህ አላቸው ቁርአን፦ ፅ #አለም፦ «አትበሉምን?» (አ ሷፋት 91) የቀረበውን ምግብ እንዲበሉት ቢነግራቸውም አልሰሙትም ምክናየቱም መስማት እና ማየት አይችሉም ሌላ ጥያቄ ጠየቃቸው። ቁርአን፦ ፅ #«የማትናገሩት ለናንተ ምን አላችሁ?» (አ ሷፋት 92) ግን መናገርም አይችሉም እንግድህ ክቡሩ የሰው ልጅ የሚያመልከው እንደዚህ የወረደ ነገር ነው የወረደ ነገር ሲያመልክ እርሱም ይዋረዳል ሀያሉን የሰማይ እና የምድርን ፈጣሪ አላህን ሲያመልክ ግን ክብሩ ይገዝፋል ማንነቱ ይከበራል። ኢብራሒምም በጣኦቶቹ ሊሰራባቸው ያሰበውን ተንኮል በጥያቄ ጀመረላቸው የማይሰሙትና የማያዩት እንድሁም የማይናገሩት የጣኦቶቹ መጨረሻ ምን ሆነ በቀጣይ ክፍል እናያለን.....
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ......
https://t.me/joinchat/AAAAAEV2Kb4hUy-9DkHbtg
#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል ስምንት
ኢብራሒም ከድንጋይ እና ከእንጨት ወደ ተፈለፈሉት ጣኦቶች ቀርቦ አናገራቸው ግን ግዑዝ ነገር ስለሆኑ

አይናገሩም እና መልስ ሊሰጡት አልቻሉም በዚህን ጊዜ ኢብራሒም ለምንድን ነው ማትናገሩት ሰዋች እንዴትስ እናተን በ አምላክነት ሊይዙ ይችላሉ በማለት በያዘው መጥረቢያ ወረደባቸው። ቁርአን፡- ፅ
#በጎይል የሚመታቸውም ሆኖ በእነርሱ ላይ በድብቅ ተዘነበለ። (አ ሷፋት 93)
አንድ ባንድ ፈላለጣቸው ከእነርሱ መካከል በጣም ትልቅ የሆነውን ጣኦት ብቻ ሳይመታ ተወው። መተው ብቻም ሳይሆን እነዚያን የፈላለጠበትን መጥረቢያ አንገቱ ላይ አደረገበት ይህንንም ያደረገበት ምክናየት ሰዋች ወደ ማምለኪያ ቦታቸው ሲመለሱ የሆነውን ሁሉ ሲያዩ ግራ እንዲጋቡ ነው። ቁርአን፡- ፅ
#ዘወር ሲሉ ስብርብሮችም አደረጋቸው። ለእነሱ የኾነ አንድ ታላቅ (ጣዖት) ብቻ ሲቀር ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)። (አል አንቢያዕ 58) ሰዋቹ ከክብረ በዐላቸው ሲተመልሰው ሲመጡ ቤተ አምልኳቸውን ሲመለከቱ ከትልቁ በስተቀር ጣኦቶቻቸው ሁሉ ተሰባብረው አገኟቸው። ትልቁ ደግሞ እርሱ የጨፈጨፋቸው በሚመስል አይነት መጥረቢያውን ከትከሻው ላይ አድርጓል። በዚህን ጊዜ በጣም በመበሳጨት ይህን ማን ሊያደርገው ይችላል በማለት ተጠያየቁ። ቁርአን ፅ
#በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራ ማነው እርሱ በእርግጥ ከበደለኞች ነው» አሉ። (አል አንቢያዕ 59)
ንግግሮቻቸውን አስተውሉ (በ አማልክቶቻችን ላይ ይህን የሰራ ማነው!?) አምላክ ከሆነ ማን በሱ ላይ ምንስ መስራት ይቻለዋል? ግን ድንቁርና አዕምሮወቻቸውን ስለዘጋው ለሚናገሩት ንግግር እንኳ አይጠነቀቁም ነበር። እናም አስከትለው ይህን የሰራው በደለኛ ነው ሊቀጣ ይገበዋል አሉ። ለፈጣሪ እንዴት ፍጡር ያግዛል ምን አቅም ኑሮት? ግን ከ ሚያመልኩት እንጨት እነሱ እንደሚሻሉ እንኳ አያውቁም። (ሰው ለ ድንጋይ ይሰግዳል!)
በዚህን ጊዜ ህዝቦች ይህን የሰራው ማን እንደሆነ መወያየት ጀመሩ በ አሳለፍነው ታሪክ ላይ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ድምፁን ቀንሶ (ዟሪወች በሆናችሁ ጊዜ በ ጣኦቶቻችሁ ላይ ተንኮል እሰራለሁ) ብሎ ሲናገር የሰሙት ሰወች ነበሩና እርሱ እንደሆነ ጠቆሙ ኢብራሒም ሚባል ወጣት በመጥፎ ሲያነሳቸው ሰምተናል እና እርሱ ሊሆን ይችላል አሉ። ቁርአን፡- ፅ
#ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው

ሰምተናል» ተባባሉ። (አል አንቢያዕ 60)
በዚህን ጊዜ ይህ የተባለው እውነት ከሆነ ለማረጋገጥ
ኢብራሒምን ካለበት ፈልጋችሁ አምጡ ተባለ። ቁርአን፡-
#ይመሰክሩበት ዘንድ በሰዎቹ ዓይን (ፊት) ላይ አምጡት»
አሉ። (አል አንቢያዕ 61)
ይህንን ጥፋት ያጠፋው እርሱ መሆኑን ሰወች ከመሰከሩበት
ለሰራው ስራ ቅጣትን ይቀጣል ብለው ተስማሙ አባቱም
ከነሱ ጋር ተባባሪ ነበር። ፍለጋው ተጠናክሮ ኢብራሂምን
ከርቀት አዩትና ወደ እርሱ እየሮጡ መጡ። ቁርአን፡- ፅ
#ወደእርሱም (ሰዎቹ) እየሮጡ መጡ። (አ ሷፋት 94)
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

https://t.me/joinchat/
AAAAAEV2Kb4hUy-9DkHbtg
#ነብዩላህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል ዘጠኝ
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) እነሱ አጠፋ ብለው ላሰቡት
ጥፋት ሰወች እንዲመሰክሩበት እና ቅጣት እንዲቀጣ
በሰወች ፊት እንዲያቆሙት ይዘውት ለመጣት ሰወች
ፍለጋ ወጡ። በፍለጋቸውም ወዳው አገኙት። ምክናየቱም
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ይህንን የሀገር ሀብት
እንድሁም አምላካችን ሚሉትን አጥፍቶ ሀገር ለቆ
አልተሰደደም እንድሁም አልተሰወረም ካለበት ሁኖ
ጠበቃቸው ወደ እርሱ እየሮጡ የመጡት ሰወችም ይዘውት
ታላላቅ ወደሚባሉት ሰወች አቀረቡት። ከዛም አሉት ቁርአን፡-
ፅ
#ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራህ አንተ
ነህን» አሉት። (አል አንቢያዕ 62)
ይህን ጥያቄ ሲያቀርቡለት ያልጠበቁትን ምላሽ ሰጣቸው፡-
ቁርአን፡- ፅ
#አይደለም ይህ ታላቃቸው ሠራው። (አል አንቢያዕ 63)
በጣኦቶቹ ላይ ይህን ጭፍጨፋ የሰራው እርሱ ታላቃቸው
ነው አላቸው። ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ይህን ለምን
አላቸው? የሰራው እርሱ ሁኖ እያለ በትልቁ ጣኦት ለምን
አሳበበ? ይህ እነርሱ ወደራሳቸው እንዲመለሱ ራሳቸውን
እንዲጠይቁ ነው ምክናየቱም ጌታ ነው ብለው ያሰቡት
ጣኦት ይሄን መስራት እና አለመስራቱን እንዴት ማወቅ
እንዳለባቸው ግራ እንዲገባቸው ለማድረግ ነው። ግራ
እንደተጋቡ ሲያውቅ ጨመረላቸው ቁርአን፡- ፅ

#ይናገሩም እንደ ኾነ ጠይቋቸው» አለ። (አል አንቢያዕ 63) ሌላኛው ትልቅ ማደናገሪያ የተጨፈጨፉትን ማን እንደጨፈጨፋቸው እንድሁም ትልቁንም ለምን እንደጨፈጨፋቸው መናገር ከቻሉ ጠይቋቸው አላቸው። ሰወቹ በጣም ግራ ተጋቡ የሚያመልኩት ነገር የማይሰማ እና የማይናገር እንደሆነ ገባቸው። ደነገጡ። ቁርአን፦ ፅ #ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ። «እናንተ (በመጠየቃችሁ) በዳዮቹ እናንተው ናችሁም» ተባባሉ። (አል አንቢያዕ 64) የኢብራሒም መልስ ራሳቸውን ስላዞረው እናተ ኢብራሒምን አንተ ነህ እንድህ ያደረከው ምናምን ብላችሁ መጠየቅ አልነበረባችሁም በማለት እርስ በእራሳቸው መጨቃጨቅ ጀመሩ። በኢብራሒም መልስ እንደተሸነፉ ገባቸው ነገር ግን በውስጣቸው ኩራት እና ድንቁርና ስላለ ማመን አልፈለጉም ወደ ራሳቸው ተመለሱና መልሰው ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) ጠየቁት፦ ቁርአን ፅ
#ከዚያም በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ። «እነዚህ የሚናገሩ አለመኾናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል፤» (አሉ)። (አል አንቢያዕ 65)
እንደማይናገሩ ድሮም እያወክ ነው ይሄንን የምትጠይቀን ሲሉ አፈጠጡበት ግን እነሱ ሳያስቡት ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ወደሚፈልገው ጉዳይ ገቡለት ኢብራሒምም አላቸው፦ ቁርአን ፅ
#ታዲያ ለእናንተ ምንም የማይጠቅማችሁንና የማይጎዳችሁን ነገር ከአላህ ሌላ ትገዛላችሁን» አላቸው። (አል አንቢያዕ 66)
መስማት እና ማየት የተሳነው መሆኑን ካወቃችሁ እንዴት ጌታ አድርጋቸው ትገዙታላችሁ ሲል አስተምሮት የሆነውን ንግግር ተናገራቸው አስከትሎም የሱም ሆነ የእነርሱ አምላክ አላህ መሆኑን አስገነዘባቸው።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....
http://t.me/AshaBuleyamine
@tafachdaewachanal
#ነብዩሏህ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል አስር
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ህዝቦቹ አምላክ ብለው የያዙት ነገር ምንም የማይጠቅም እና የማይጎዳ መሆኑን እርምጃ ወስዶም ቢያሳያቸው ሊያምኑለት አልቻሉም በዚህን ጊዜ ለእነርሱም ሆነ አምላካቻን ለሚሉት ድንጋይ የማጥላላትን ቃል ተናገራቸው ቁርአን፦ ፅ

#ፎህ! (ኤጭ) ለእናንተ ከአላህ ሌላ ለምትገዙትም ነገር፤ አታውቁምን» (አለ)። (አል አንቢያዕ 67)
ይህንን ቃለ ምልልስ ካደረጉ በኋላ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ለ ጣኦቶቹ ያላቸውን ጥላቻ ሲያዩ ጣኦቶቹን እርሱ እንደሰባበራቸው ርግጠኛ ሆኑ። እነዚያ የድንጋይ ቁርጥራጮች ራሳቸውን ለመከላከል አንዳች ነገር ማድረግ አለመቻላቸውን አስተውለው ወደ እውነት በመመለስ ፋንታ በ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ላይ ክፉ ነገር አሰቡ።
እንድህ አሉም ቁርአን፦ ፅ
#ሠሪዎች እንደ ኾናችሁ አቃጥሉት። አማልክቶቻችሁንም እርዱ» አሉ። (በእሳት ላይ ጣሉትም)። (አል አንቢያዕ 68)
በዚህም ሁኔታ ላይ ሳሉ መጀመሪያ ወደ ንጉሱ መውሰድ እንዳለባቸው ተረዱ ከዚያም ጣኦት ተገዢወቹ ለንጉሱ ኑምሩዝ ሁኔታውን ተረኩለት። ኑምሩዝ ኢብራሒምን አስጠራቸው። በደንባቸው መሰረት ማንኛውም ሰው ወደ ኑምሩዝ ሲገባ ለእርሱ ይሰግዳል። ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሲገቡ አልሰገዱለትም ነበር። ኑምሩዝ ኢብራሒም ለምን እንዳልሰገዱ ጠየቃቸው። ኢብራሒም አንተንም እኔንም ለፈጠረን አምላክ እንጅ አልሰግድም አሉት። ኑምሩዝም አላቸው፦
ጌታህ ማነው!?
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) መለሱለት፦
ቁርአን፦ ፅ
#ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው ሰው አላየህምን ኢብራሂም «ጌታዬ ያ ሕያው የሚያደርግና የሚገድል ነው» ባለ ጊዜ (አል በቀራህ 258)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የኔ ጌታ ህይወትን የሚሰጥ እና የሚገድልም ነው አሉት እርሱም ተከታዩን መለሰ
ቁርአን፦ ፅ
#እኔ ሕያው አደርጋለሁ እገድላለሁም» አለ። (አል በቀራህ 258)
በትቢት ተሞልቶ ሁለት ሰወችን ከእስር ቤት አስመጣ

ከዚያም አንዱን ኢብራሒም እያዩ ገደለው ሁለተኛውን ደግሞ በነፃ አሰናበተው። ከዚያም ለኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አየህ እኔም ይህን ማድረግ እችላለሁ አላቸው። ኑምሩዝ ግን አልገባውም ኢብራሒም ስለ አላህ የነገሩት ምንም ያልነበረን ነገር ህይወትን መስጠት እንደሚችል እና ህይወት ያለውንም ነገር መግደል እንድሁም ድጋሜ መቀስቀስ እንደሚችል ነው እርሱ ግን ኢብራሒምን ለመከራከር እና በሰወች ዘንድ ጌትነቱን ለማሳወቅ ነበር ግን ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የመጀመሪያው ባይገባውም ሳያብራሩለት ለእርሱም ለሰወችም ግልፅ የሆነን ጥያቄ አቀረቡለት፦

#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

http://t.me/AshaBuleyamine
@tafachdaewachanal
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_አንድ

ኑምሩዝ የጌትነት ፉክክሩን እንደቀጠለ ነው ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) አላህ እንደሚገል እና ህያው እንደሚያደርግ በነገሩት መሰረት እርሱም እኔም ይህን ማድረግ እችላለሁ በማለት ሁለት ሰወችን አምጥቶ አንዱን በመግደል አንዱን ነፃ በመልቀቅ የሞኝ ቀልዱን ቀልዷል ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ይህንን ለቀልድ ያመቸውን ጥያቄ በመተው ሌላን ጥያቄ ጠየቁት አሉት፦ ቁርአን ፩ #ኢብራሂም፦ «አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል (አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት» አለው። (አል በቀራህ 258)

በዚህን ሰአት ደነገጠ ለሰወች ማስመሰል እንኳ በማይችልበት ጥያቄ መጡበት ፀሀይን አይደለም በምዕራብ ሊያስወጣት ቀርቶ ሙቀቷን እንኳ ተቋቁሞ መኖር አይችልም በዚህም ምክናየት በክርክሩ ተሸነፈ። ቁርአን፦ ፩ #ያም የካደው ሰው ዋለለ፤ (መልስ አጣ) አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም። (አል በቀራህ 258) አላህ በዳይ ህዝቦችን አይመራም ሲል አላህ ተናገረ። በዳይ ህዝቦች ጥመትን እንጅ እውነተኛን ጎዳና መመራት አይችሉም ልቦቻቸው ላይ ሀቅን ለመቀበል የማያስችል ኩራት አለባቸው።

ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ክርክሩን በዚህ መልኩ ሲረቱት በጣም ተበሳጨ በዚህን ጊዜ ምን አይነት እርምጃ

እንደሚወሰድበት አማካሪወቹን ጠርቶ አማካረ። እንዴት አድርገን እንቅጣው በማለት ጠየቃቸው። ከሰወች መካከል አንዱ ተነስቶ በእሳት እናቃጥለው አለ። ሀሳቡም ተቀባይነትን አገኘ። ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) ለማቃጠል ዝግጅት ተጀመረ። አንድ ወር ሙሉ ያለማቋረጥ የሚቀጣጠል እንጨት ሰብስቡ አሉ። ብዙ እንጨትም ተጋዘ።
እንደተራራ በተቆለለው እንጨት ላይ እሳት ለቀቁበት። ነበልባሉ ሰማይ ድረስ ወጣ። በተፈጠረው ከፍተኛ ሙቀት ምክንያት አዕዋፋት በ አካባቢው መብረር አልቻሉም። ዝግጅታቸውን ሁሉ ካጠናቀቁ በኋላ እሳቱ በደንብ መንቀልቀል ሲጀምር ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) አመጡ። እጆቻቸው በሰንሰለት ተጠፍረዋል። እግሮቻቸውም እንድሁ በእግር ብረት ታስረዋል።
እኚህ ታላቅ ነብይ የ አላህ (ሁብሀነሁ ተዐላ) ትልቅ ወዳጅ ለ አላህ ትዛዝ እጅ ሰጥተዋል። በ አላህ ተመክተዋል። ሁኔታው ቢያስፈራም ቅንጣት ድንጋጤ ወይም ሽብር ውል አላለባቸውም።
ወደ እሳቱ ካቀረቧቸው በኋላ እንዴት ሳቱ ውስጥ እንደሚያስገቧቸው አሳሰባቸው ምክናየቱም እሳቱ ሰውን አያስቀርብም ነበር በጣም ከባድ የሆነ እሳት ነው። በዚህን ጊዜ ኑምሩዝ አማካሪወቹን ሰብስቦ አማከረ። ከዚያም በወስፈንጥር ተጠቅመው እንዲያስወነጭፏቸው ተስማሙ። በዚህን ጊዜ በሰማይም በምድርም ያሉ መላኢኮች ተሸበሩ። ወደ አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ተዋደቁ። ጌታቸውን ተማፀኑ።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....
http://t.me/AshaBuleyamine
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_ሁለት
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ወደ እሳት ሊወረወር ሰወች በዝግጅት ላይ በሆኑ ጊዜ መላኢኮች ተሸበሩ። ወደ አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) በመዋደቅ ተማፀኑ።
ያ ለጢፍ ያ አላህ! ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) ወደ እሳት ሊወረውሩት እኮ ነው አንተን ከማውሳት የማይዘነጋው ነብይ በእሳት ሊቃጠል ነው ፍቀድልንና እንርዳው አሉት። አላህም ፈቀደላቸው። መላኢኮችም ወደ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) መጡ።
አንደኛው መላኢካ ለ ኢብራሒም እንድህ አለው፦
 እዘዘኝና በንፋስ እሳቲቱን ብትንትኗን አወጣታለሁ!

ሌላኛውም መለኢካ እንድህ አለ፦
እዘዘኝ። ውሃን ማዘዝና በቅፅበት እሳቷን ማጥፋት እችላለሁ!
ሌላኛውም አለ፦
እዘዘኝ። መሬትን አዛታለሁ ከፈለክ እሳቷን እንድትውጣት አደርጋለሁ!
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የነዚህን የ አላህ ሰራዊትወች ንግግር ከሰሙ በኋላ እንድህ በማለት መለሱላቸው፦
በወዳጆች መካከል ጣልቃ አትግቡ! እኔ የ አላህን ውሳኔ ተቀብያለሁ! ነፃ ካወጣኝ ከእዝነቱ ነው! እንድቃጠል ከተወኝ የፈፀምኩት ሀጢያት ቢኖር ነው! ኢንሸ አላህ እታገሳለሁ!.....
ከዛም ወደ እሳቱ ሊወረውሯቸው ልብሳቸውን አስወልቀው ከወስፈንጠሩ ላይ አስቀመጧቸው። በዚህን ጊዜ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ይችን ንግግር ነበር ሚደጋግሙት፦
(አላህ ብቻ በቂየ ነው፣ በእርሱ መመካት እንዴት ያምር!)
በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁነው እሳቱ ላይ ሊጣሉ ደቂቃወች ሲቀራቸው ጅብሪል (ዐለይሂ ሰላም) መጣ ከዛም ጠየቃቸው፦ የምትፈልገው ነገር የለም? ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) የምፈልገው አለኝ። በማለት መለሱለት ከዛም አስከትለው ግን ፍላጎቴ ካንተ ዘንድ አይደለም! ጀብሪል (ዐለይሂ ሰላም) በመገረም ጠየቃቸው፦ ለምን አላህን (ሱብሀነሁ ተዐላ) ከዚህ ካለህበት ችግር እንዲያወጣህ አጠይቀውም?
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) እንድህ በማለት መለሱለት፦
እርሱ ያለሁበትን ሁኔታ ከማንም በላይ ያውቃል! እስኪ ንገረኝ፣ እሳት በማን ትዕዛዝ ነው የምትቀጣጠለው? ማቃጠሏ በማን ቁጥጥር ስር ነው? ጅብሪልም (ዐለይሂ ሰላም) በ አላህ ሲል መለሰላቸው ስለዚህ አላህ ያውቃል አላህ በቂየ ነው በእርሱ መመካት እንዴት ያምር አሉ።
ይህ እንግድህ የ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በ አላህ ላይ ያላቸውን ጠንካራ እና የማይላላ ተወኩል ያመላክታል።
ከማንም በላይ በአላህ መደገፍ እንዳለብን ከኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ታሪክ እንማራለን ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ይህ ተወኩላቸው ከ አላህ ምን አበረከተላቸው የፅናታቸውስ መጨረሻ ከምን አደረሳቸው በቃጣይ ክፍል እናየዋለን።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

@Sunatube
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_ሶስት
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ፍፁም ወደ አላህ በመዋደቃቸው በእርሱ ብቻ በመመካታቸው እሳቱ ውስጥ ከመጣላቸው በፊት ከ አላህ ዘንድ ትዛዝ መጣ። ቁርአን፡-
á
#እሳት ሆይ! በኢብራሂም ላይ ቀዝቃዛ፤ ሰላምም ሁኚ» አልን። (አል አንቢያዕ 69)
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) መላኢካወች የመላኢካወቹ ሁሉ አለቃ ጅብሪል ሳይቀር ልርዳህ ሲላቸው በጭራሽ አልፈልግም አሉ። ከ አላህ ብቻ ነበር እርዳታን የፈለጉት። አላህም እሳቱ ሳይጠፋ ለሰወች የሚያቃጥል እና የሚነድ ሲሆን ለ ኢብራሒም ግን ቀዝቃዛ እና ሰላም እንድትሆን ታላቁ አላህ አዘዛት። እሳትም የ አላህ ፍጡር ናትና ትዛዙን ተቀብላ ቀዝቃዛ እና ሰላም ሆነች። አላህ ቀዝቃዛ ብቻ ሁኚ ቢለት ኢብራሒም በብርድ ይጎዳ ነበር ነገር ግን ምቹ እና ተስማሚ ሁኔለት ሲል አዘዘ። በትዛዙም መሰረት ሆነች። ኢብራሒምም ወደ እሳቱ ተወረወሩ የወደቁበት ቦታ ወዳው ወደ አትክልትነት ተቀየረ። እዚያው ላይ ደግሞ ምንጭ ፈለቀች እና ውሃዋ ኮለል ብሎ ፈሰሰ። ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) እጃቸው እና እግራቸው ተጠፍሮ የታሰረበት ማሰሪያ በእሳቲቱ ተቃጥሎ ከሰውነታቸው ሲረግፍ አካላቸውን ግን ማቃጠል አልቻለችም ነበር። አላህ ትልቅ በሆነው ተዐምሩ አዳናቸው።የ አላህ ጠላቶች እና ኑምሩዝ ባዩት ነገር በጣም ተገረሙ በዚህን ጊዜ ኑምሩዝ በጣም ከመደነቁ የተነሳ ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) እንድህ አላቸው፡- ለ አምላክህ ክብር ብየ አራት ሺ ከብቶቺን አርዳለሁ!
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) እንድህ በማለት መለሱለት፡- ከጥመትህ ተመለስ። ወደ ተውሒድ እስካልተመለስክ ድረስ በርካታ ከብቶችን ማረድህ ዋጋ የለውም!
ኑምሩዝም አለ፡- ስልጣኔንና እና ንግስናየን መስዋት ማድረግ አልችልም። ነገር ግን ለክብሩ ስል አርዳለሁ! በእርግጥም አራት ሺህ ከብቶችን አረደ። እንዲሁም ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) ማሳደዱን አቆመ። ነገር ግን በትዕቢቱ በመሸንገሉ እና በድርቅናው ምክናየት ቅኑን ጎዳና ከተከለከሉት እድለ ቢሶች መካከል ሆነ። ከጎሳው ውስጥ የተወሰኑ ሰወች ከጣዖት አምላኪነት ወጥተው ወደ እምነት

መጡ። ግልፅ በሆነው ተዐምር ሰበብ ተውሂድን አወቁ።
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) እሳቱ ነዶ እስከሚያልቅ ድረስ
እዛው ቆዩ ሶስት ቀን ሰባት ቀን ወይንም አርባ ቀን
እንደቆዩ ይነገራል። ከቆይታቸውም በኋላ ከእሳቱ በሰላም
ወተው ከህዝባቸው ጋር ተቀላቀሉ።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

http://t.me/AshaBuleyamine
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_አራት
#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ከእሳቱ አላህ ነፃ ካወጣቸው
በኋላ ዳዕዋቸውን ቀጠሉ ህዝቦቻቸውን ከባዕድ አምልኮ
ማስጠንቀቁን ከበፊቱ በበለጠ ቀጠሉበት።
እናም ከ አላህ ሌላ አማልክት መያዛቸው በዱኒያ ላይ ሳሉ
ለመዋደድ እና ለመጠቃቀም መሆኑን አስረግጠው ነግረው፦
በመጨረሻውም አለም አንዱ አንዱን እንደሚክድና
መጨረሻቸው እና መኖሪየቸው እሳት እንደሆነች
አረጋገጡላቸው። ዛሬ ላይ ረዳት እና አጋዥ አድርገው
ቢይዟቸውም የውሸት ረዳት መሆናቸውን ወደፊት ያለ ረዳት
እንደሚቀሩና እነርሱም ምንም የማይረዷቸው መሆናቸውን
አረዷቸው ምንም እንኳ እነርሱ አሁን ላይ መርዶ መስሎ
ባይታያቸውም። ቁርአን የኢብራሒምን ንግግር እንድህ
አስፍሮታል á
#ኢብራሂም አለም «ከአላህ ሌላ ጣዖታትን (አማልክት)
የያዛችሁት በቅርቢቱ ሕይወት በመካከላችሁ ለመዋደድ ብቻ
ነው። ከዚያም በትንሣኤ ቀን ከፊላቸሁ በከፊሉ ይክዳል።
ከፊላችሁም ከፊሉን ይረግማል። መኖሪያችሁም እሳት ናት።
ለእናንተም ከረዳቶች ምንም የላችሁም።» (አል አንከቡት
25)
ኢብራሒምም (ዐለይሂ ሰላም) በዚህ የዳዕዋ ጥሪያቸው
ነብዩሏህ ሉጥ (ዐለይሂ ሰላም) ካመኑት ውስጥ አንዱ
ነበሩ። ሉጥ (አለይሂ ሰላም) አመኑ ሲባል መጀመሪያ
ከሀዲ ነበር እንዴ? ከሀዲስ የነበረ ሰው ነብይ እንዴት
ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ነገሩ
እንድህ ነው፦ ሉጥ (ዐለይሂ ሰላም) የኢብራሒም (ዐለይሂ
ሰላም) የወንድም ልጅ ነው። እናም ሉጥ (ዐለይሂ
ሰላም) ከበፊቱም በ አላህ የሚያምኑ ሰው ነበሩ። ይህ
በእንድህ እንዳለ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ነብይ
ተደርገው ለ #ኪልዳን ህዝቦች ሲላኩ ነብዩሏህ ሉጥ

(ዐለይሂ ሰላም) የኢብራሒምን ነብይነት ካፀደቁት እና ከተቀበሉት ሰወች የመጀመሪያው ነበሩ ለማለት ነው። አላህ እንድህ ይላል ቁርአን፦ ፅ
#ሉጥም ለእርሱ አመነ፤ (አል አንከቡት 26)
ይህ የቁርአን አንቀፅም በግልፅ ያብራራዋል ሉጥ ለእርሱ አመነ የኢብራሒምን ነብይነት ተቀበለ ማለት ነው።
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሉጥን ጨምሮ ያመኑትን ሰወች ይዘው እንዲሰደዱ #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) አዘዛቸው። በኪልዳን ጎሳ እና በ አመፀኛው ኑምሩዝ ላይ ከሚልከው ቅጣት ይድኑ ዘንድ እንዲሁም እርሱን በነፃነት ያመልኩ ዘንድ ፈቀደላቸው። በዚህ መልኩ #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ወዳጁን ኢብራሂምን (ዐለይሂ ሰላም) እና አማኞችን ከ ጨቋኞች ገላገላቸው።
እንድሁም ኑምሩዝ እና ከሀዲያኖች ከባድ የሆነን ቅጣት ቀጣቸው። እንዴት እንደጠፉ በቀጣይ ክፍል እናያለን፦
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ....

@tafachdaewachanal

#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_አምስት
የኪልዳን ህዝቦች ብዙው ኮከብ አምላኪ ሲሆን እንድሁም አመፀኛውን ኑምሩዝን ሚያመልክም አልጠፋም እርሱም አምላክ ነኝ በማለት ቂሎችን በማቄል ወደ እሳት ይነዳቸዋል ወደ ትልቋ እሳት (ጀሀነም)በጥመታቸው በበረቱም ጊዜ ቅጣቱ መጣባቸው የ አላህም ቅጣት በመጣ ጊዜ ለእርሱ መላሽ ከ አላህ በስተቀር የለም።
እነዚህን ጠጋበኞች ለማጥፋት #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) በመላኢኮች ወይንም በመሬት መንቀጥቀጥ ወይንም በድርቅ አልነበረም ያጠፋቸው። የትንኝ መንጋወችን ነበር የላከባቸው። ሁሉን አውቃለሁ እችላለሁ የሚለው የሰው ልጅ እንድህም በደካማዋ ትንኝ ይጠፋል። የትንኙ መንጋ እንደ አቧራ ነበር የወረደባቸው። ትንኞቹም ጣኦት አምላኪና ትዕቢተኛ የሆኑትን በሙሉ ስጋቸውን ካጥንታቸው በመለየት ጭንቅላታቸውን ባዶ በማድረግ በቀያቸው ረግፈው እንዲቀሩ አደረጉ። ኑምሩዝ ለተባለው ባለፀጋ እና ጠጋበኛ #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ሀያልነቱን ሊያሳየው እንድሁም ከሰው የበታች አድርጎ ሊያዋርደው አንድትን ትንሽ ብቻ ላከበት እርሷም በአፍንጫው ውስጥ ገብታ ጭንቅላቱ ድረስ

ዘለቀች። ራሱንም በጣም ያመው እና ህመሙንም መቋቋም አቃተው። በ ጭንቅላቱ ውስጥ እየተንሸራሸረች ረፍት ነሳችው። ያ ባለ ፀጋ በሀገሪቱ የተከበረ ሰው ትንሿ ጭንቅላቱ ውስጥ ከገባች ጀምሮ እርሱ ዘንድ በላጭ ሰው ማለት የሱን ጭንቅላት ያለ ማቋረጥ ሚደበድብ ነበር። ህመሙ ሲያሰቃየው ጭንቅላቱን ሲደበድቡለት ነበር ትንሽ እንኳ ረፍት ሚያገኘው። በዚህም ህመም ለብዙ አመት ተሰቃይቶ መጨረሻ ላይ ጭንቅላቱ ተሰንጥቆ ለህልፈት በቃ። ብዙ ጊዜ አመፀኛ ሰወች መጨረሻቸው የሚያስጠላ እና የሚዘግንን ነው መጨረሻቸውም ጀሀነም መውረድ ነው እነርሱም ሲያቄሏቸው የነበሩትም ህዝቦች እንድሁም ሲያመልኳቸው የነበሩት ጣኦት አብረው ይማግዳሉ።
የኪልዳን ህዝቦች ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሰወችን ወደ ተውሂድ ፦ ባሮችን ከመገዛት ባሮችን ወደፈጠረው #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) አምልኮ ለእርሱ እንጅ ለማንም እንደማይገባ እንድሁም ጣኦትን ከመገዛት ጨለማ #አላህን (ሰብሀነሁ ተዐላ) ወደ መገዛት ብርሀን ጠሯቸው። ነገር ግን አንቀበልም ማለታቸው ሳያንስ በኢብራሒም ላይ ተንኮልን መሸረብና እሳት ውስጥ እስከመጣል አደረሷቸው በዚህም ጊዜ #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) መጨረሻቸው
የትንኝ ምግብ እንዲሆኑ ወሰነባቸው። ቁርአን፦ ፅ #በእርሱም ተንኮልን አሰቡ። በጣም ከሳሪዎችም አደረግናቸው። (አል አንቢያዕ 70)
እንድሁም ኢብራሂምን እና ሉጥን እና አማኞችንም እንዲሰደዱ በመፍቀድ እንዳዳናቸው #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ይናገራል ቁርአን፦ ፅ #እርሱንና ሉጥንም ወደዚያች፤ በውስጧ ለዓለማት በረከትን ወደ አደረግንባት ምድር (በመውሰድ) አዳን።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል ....

https://t.me/joinchat/AAAAAEV2Kb4hUy-9DkHbtg
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_ስድስት
የኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ስዴት ቁርአን፦ ፅ #ኢብራሂም «እኔ ወደ ጌታዬ ተሰዳጅ ነኝ። እነሆ እርሱ አሸናፊው ጥበበኛው ነውና» አለም። (አል አንከቡት 26)
#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ከ ባቢሎን ወደ ሂራን ተሰደዱ። ባቢሎን ከ ኡረፋ በስተደቡብ ነበረች።

የወንድማቸው ልጅ ሉጥ እና ትቂት አማኞች እዚያ ድረስ ሸኟቸው።
#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በ #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ትዕዛዝ የ አጎታቸው ልጅ የሆነችውን ሳራን አገቡ። ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሚስታቸውን ሳራን ይዘው ወደ ሻም ሔዱ። ከዚያም ወደ ሚስር (ግብፅ) ተሻገሩ። ነብዩሏህ #ሉጥ (ዐለይሂ ሰላም) በበኩላቸው ወደ ሰዶም ህዝቦች ተሰደዱ። ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሚስታቸውን ሳራን ይዘው ግብፅ ሀገር ገቡ። ግብፅ ያኔ መሪወቿ በዳይወች እና ትዕቢተኞች ነበሩ። በዚህም የተነሳ አንድ ባህል ነበራቸው። አንዲት የሌላ ሀገር እንስት ወደ ከተማቸው ስትገባ ቆንጆ ከሆነች በፍጥነት ለ መሪያቸው ይነግሩታል። ባለ ትዳር ከሆነች ባሏን ይገድሉባታል። አብሯት ያለው ወንድሟ ከሆነ ደግሞ እንዲድርላቸው ይጠይቁታል። ታዳ በዚህ ክፉ ጊዜ ነበር #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ከ ሚስታቸው ሳራ ጋር ግብፅ የገቡት። ከተማዋም ሲገቡ ወዲያውኑ ወሬያቸው ከ ንጉሱ ዘንድ ደረሰ። አንዲት ቆንጆ ወደ ከተማዋ መግባቷ ተነገረው። የንጉሱ ወታደሮች ቆንጆዋን ሴት ከ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ጋር ነበር እና ያዩዋት ኢብራሒምን ምናቸው እንደሆነች ከእርሷ ጋር ስላላቸው ግንኙነት ጠየቋቸው። #ኢብራሒምም (ዐለይሂ ሰላም) እህቴ ናት አሏቸው። ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ይህንን ሲሉ በውስጣቸው የእምነት እህቴ ናት ማለትን አስበው ነበር። በዚህ ሰበብ ምክናየት ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ላይ ምንም ጉዳት ሳያደርሱባቸው ቀሩ። ነገር ግን ሳራን ለንጉሱ ወደ ቤተ መንግስት ወሰዷት።
የዚህን ታሪክ ዝርዝር ቡኻሪ ከ አቡ ሁረይራ (ረድየሏሁ አንሁ) በተያዘ ሀዲስ የአላህ መልክተኛ እንድህ ሲሉ ይተአትሹምብኝ።#ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሳራን ይዘው ተሰደዱ። ከንጉሶች ሁሉ አንድ ንጉስ ወይም ከ አንባገነኖቹ አንዱ አንባገነን ከሚኖርበት መንደር ደረሱ። ያ አምባ ገነን ንጉስ ለሱ ሰወች አሉት አንድ ሰው በጣም ውብ የሆነች ሴት ወደከተማዋ ይዞ ገባ። ንጉሱም ወደ #ኢብራሒም መልዕክተኛ ላከ፦ መልዕክተኛውም አንተ ኢብራሒም ሆይ! ካንተ ጋር ያለችው ሴት ምንህ ናት ተባለ። ኢብራሒምም እህቴ ናት አሉ። ወደእርሷም ዞሩና እንድህ አሏት፦ እህቴ ናት ብያቸዋለሁ እና እንዳታስተባብይ። ወላሂ ከእኔ እና ካንች ውጭ በምድር ላይ ሌላ አማኝ የለም። ከዚያም ወደ ንጉሱ ላኳት። ሳራ ከቤተ መንግስቱ

እንደደረሰች ውዱዕ አድርጋ እንድህ በማለት ዱአ አደረገች፦
#አላህ_ሆይ! እውነት ባንተ እና በመልክተኛህ አምኜ ከሆነ፣ ብልቴንም ለባሌ እንጅ ጠብቄ ከሆነ፣ ከሃዲ በላዬ ላይ አትሹምብኝ።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

http://t.me/AshaBuleyamine
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_ሰባት
#አላህ_ሆይ! እውነት ባንተ እና በመልክተኛህ አምኜ ከሆነ፣ ብልቴንም ለባሌ እንጅ ጠብቄ ከሆነ፣ ከሃዲ በላዬ ላይ አትሹምብኝ።
ሳራ ይህንን ዱአ አድርጋ ወደ ቤተ መንግስቱ ገባች።
ንጉሱም ወደ እርሷ ዘንድ ሲገባ ሊቀርባት አልቻለም። እግሩ ተዝለፍልፎ እስኪወድቅ ድረስ በእንቅልፍ ተረታ።
እርሷም፦ ጌታዬ ሆይ! (ይህ ሰው) ከሞተ ገደለችው እባላለሁ በማለት አላህ ያነቃው ዘንድ ዱአ አደረገች።
በዚህን ጊዜ አላህ እንዲነቃ አደረገው። ከዚያም በነቃ ጊዜ አሁንም ወደ እርሷ አሰበ። ሳራ አሁንም እንድህ ስትል ዱአ አደረገች፦ ጌታዬ ሆይ! እውነት በ አንተ እና በመልክተኛህ አምኜ ከሆነ ብልቴንም ለባሌ እንጅ ጠብቄ ከሆነ፣ ይህን ከሃዲ በላዬ ላይ አትሹምብኝ። በዚህ ጊዜ ሰውየው በድጋሜ ተዝለፍልፎ እስኪወድቅ ድረስ በእንቅልፍ ተረታ። አሁንም ጌታዬ ሆይ! ይህ ሰው ከሞተ ገደለችው እባላለሁ>> ስትል በድጋሜ አላህን ለመነች። ንጉሱ አሁንም በድጋሜ ነቃ እንደዚሁ ሶትስት ጊዜ ሆነ።
በመጨረሻም እንድህ አለ፦ በጌታዬ እምላለሁ። ይህች ሴት ሰይጣን እንጅ ሰው አይደለችም። ወደ ኢብራሒም ውሰዷት።
>> ከባሮቹ አንዷን #ሀጀር ምትባለዋን ስጧትና ትሂድ አለ ከዚያም ወደ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ተመለሰች።
እንድህም አለች፦ #አላህ ከሀዲን አስገድዶ ሴቷን ልጅ እንዴት እንዳስመቻት አየህ? (ቡኻሪ አል ቡዩዕ 100 ፣ አህመድ 2:403)
እናታችን ሳራ ከ ባዕድ ወንድ ብልቷን በመጠበቋ እንዲጠብቅላትም ወደ አላህ በዱአ በመዋደቋ አላህ በዚህ መልኩ አዳናት እንድሁም ሀጀር የምትባለዋን ሴት ሸልማት ተሰጠች ሀጀር የ ኢስማኢል (ዐለይሂ ሰላም) እናት ስትሆን የነብዩ ሙሀመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የዘር ሀረግ ከ ኢስማኢል ከ ሀጀር ልጅ ይመዘዛል።

ወደ አላህ የሸሸ እና መጠጊየውን እርሱን ያደረገ መጨረሻው የተዋበና ያማረ ይሆናል #አላህም (ሱብሀነሁ ተዐላ) ከእነዚህ ሰወች ጋር ነው። ቁርአን፡- ፩ #እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በመታገስና በሶላት ተረዱ። አላህ (በእርዳታው) ከታጋሾች ጋር ነውና። (አል በቀራህ 153) በተጠቀሰው አንቀፅ መሰረት የእናታችን ሳራ ሶላት እና ፍፁም ወደ አላህ መጠጋት ውጤቱ ከንጉሱ ነፃ መውጣት ነበር። መታገስ እና ነገሮች እየሆኑ ያሉት ለኸይር ነው ብሎ ማሰብ እና ወደ አላህ መጠጋት በመጀመሪያ እየሆነ ካለው ነገር ድንበር ያለፈ ጭንቀት እና ፍርሀት እንዳይሰማን ይረዳናል ሲቀጥል #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) በታገስንበት ትዕግስት በአኼራ ትልቅ አጅርን ይሰጠናል በ አዱኒያም ሳለን የታገስንበትን ነገር ይተካልናል እርሱ በነገራችንም ሁሉ ላይ ከእኛ ጋር ይሆናል።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

http://t.me/AshaBuleyamine
#ነብዩሏህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_ስምንት
እናታችን ሳራ ከዚህ ጭንቅና ፈተና በ #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ፍቃድ ነፃ ከወጣች በኋላ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሳራን እና ሀጀርን ይዘው ወደ ፍልስጤም ተመለሱ። ጓዛቸውንም "ሰበዕ" ተብሎ በሚጠራ ምድረ በዳ አኖሩ። ውሃ ያስፈልጋቸው ነበር እና ጉድጓድ መቆፈር ጀመሩ። በ አላህ ፍቃድ ኮለል ያለ ውሃም ወጣላቸው።
ከጊዜ በኋላ ውሃ እና ስንቃቸው ሲያልቅ ወደ ከተማዋ አቅጣጫ ጉዞ ጀመሩ። ትንሽ እንደተጓዙ ምንም ገንዘብ እንደለላቸው አስታወሱና ወደመጡበት ተመለሱ።
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሲመለሱ ሳራ እና ሐጀር ሚሰራ ምግብ ይዘው ይመጣሉ ብለው ስለሚጠብቋቸው ምንም ነገር ስላላገኙ ከረጢታቸውን በ አሺዋ ሞልተው ወደ ቤት ሄዱ። ይህንንም ያደረጉት ሳራ እና ሐጀር ተስፋ በመቁረጥ እንዳይጎዱ በማሰብ ነበር። ተመልሰው ከመጡ በኋላ ድካም ስለተሰማቸው በ አሺዋ የተሞላውን ከረጢት አስቀምጠው ገብተው ጋደም አሉ እንቅልፍ ወሰዳቸው።
ሳራም ለ ሐጀር ከረጢቱን ክፈችው አለቻት፡- ሐጀርም ስትከፍተው ስንዴ ነበር። ወዳው መፍጨት ጀመሩ። ቂጣ ጋገሩ። #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ባዩት ነገር ተገረሙ። #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ)

እንደረዘቃቻው አወቁ ለምስጋናም ወደ ጌታቸው ዞሩ።
አላህን አመሰገኑ።
"ሰበዕ" አካባቢ በረካው በዛ። ፀጋው በረከተ። በርካታ ሰወችም ወደ አከባቢው በመምጣት ሰፈሩ። ቦታው በሰወች ተሞላ። ከጊዜ በኋላ ግን ኗሪወቹ ክህደት ውስጥ ገቡ።
#ኢብራሒን (ዐለይሂ ሰላም) በእጃቸው ቆፍረው ካወጡት ውሃ እንዳይጠቀሙ ከለከሏቸው። የ አላህ ወዳጅ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በጣም ተጎዱ። በዚህም በጣም አዘነው ነበር እና ውሃው ደረቀ። ሰወቹም ጥፋታቸው ገባቸው እና ተፀፀቱ። ወደ ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በመምጣትም ይቅርታ ጠየቋቸው። #አላህን ምህረት እንዲለምኑላቸውም ተማፀኗቸው። ታጋሹ ነብይም ይቅርታቸውን ተቀበሉ። ኢብራሒምም (ዐለይሂ ሰላም) ወደ አላህ ዱአ አደረጉ። አላህም ራህመቱን ዳግም አፈሰሰው። ውሃው በረከተማፀኑት። #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ከጌታቸው ተዐምራቶች አንዱ የሆነውን ሙታንን የማስነሳት ድንቅ ብቃቱን ማየት ፈለጉ። አላህንም ጌታየ ሆይ! ሙታንን እንዴት እንደምትቀሰቅስ አሳየኝ ሲሉ ተማፀኑት። ቁርአን፡- ፩
#ኢብራሂምም «ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ።) (አል በቀራህ 260)
#አላህም (ሱብሀነሁ ተዐላ) #ኢብራሒምን (ዐለይሂ ሰላም) እንግዳ የሆነን ጥያቄ ጠየቃቸው፡- ሙታንን ህያው ማድረግ እንደምችል አላመንክም እንዴ አላቸው። ቁርአን፡- ፩
#አላህ ፡- «አላመንክምን» አለው። (አል በቀራህ 260)
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....

http://t.me/AshaBuleyamine
#ነብዩላህ_ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም)
#ክፍል_አስራ_ዘጠኝ
ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) #አላህ (ሱብሀነሁ ተዐላ) ሙታንን ህያው ማድረግ እንደምችል አላመንክም እንዴ ብሎ ሲጠይቃቸው፡- የኢብራሒምን መልስ አላህ በቁርአን እንድህ ነበር ያስቀመጠው ቁርአን፡- ፩
#አይደለም (አምኛለሁ)፤ ግን ልቤ እንዲረጋ» ነው አለ።
(አል በቀራህ 260)

የ አላህ ነብይ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) ሙቶ በመቀስቀስ ተጠራጥሮ ወይንም የ አላህ ችሎታ ጭንቅላቱ ውስጥ ጥያቄ ፈጥሮበት ሳይሆን አላህ ሙታንን እንዴት ህያው እንደሚያደርግ ችሎታውን በ አይኑ ማየት ነው የፈለገው። #አላህም (ሱብሀነሁ ተዐላ) ከበራሪወች አራትን እንዲይዙ አዘዛቸው። ቁርአን፡- á #አላህም)፡- «ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ። ወደ አንተም ሰብስባቸው። (ቆራርጣቸውም)፤ ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁራጭን አድርግ። ከዚያም ጥራቸው፤ ፈጥነው ይመጡሃልና። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ መኾኑን እወቅ። (አል በቀራህ 260)
ኢብራሒም አራቱን በራሪወች አረዷቸው። ከዚያም ሁሉንም ቆራረጧቸው ስጋቸውን ቀላቀሉት አብረው ፈጩት የ አራቱም አዕዋፋት ስጋ እና አጥንት ተፈጭቶ በ አንድ እቃ ላይ ሆነ። ከዚያም #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) በታዘዙት መሰረት ስጋውን በ አራት ተራራወች ላይ አስቀመጡ። የ አዕዋፎቹን የተቆረጠ አንገታቸውን ይዘው ኑ ሲሉ ጠሯቸው። በዚህን ጊዜ አራቱም ተራራ ላይ ያለው የተፈጨ ስጋ በሰማይ ላይ እየበረረ አንዱ ካንዱ ጋር እየተሰባጠረ #ኢብራሒም በ አይናቸው እያዩ ወፍ መሆን ጀመረ። አራቱም አንገት የለላቸው በራሪወች ወደ #ኢብራሒም (ዐለይሂ ሰላም) መጡ። ኢብራሒም የ አንዱን በራሪ አንገት ለሌላኛው ሲሰጡት አልሰካ ይላቸዋል። ትክክለኛውን የራሱ የሆነውን አንገት ሲሰጡት ይሰካል ። በዚህ አይነት ተዐምር አራቱም ተቆራርጠው ስጋቸው የተቀላቀለው በራሪወች እንደገና ወደ ማንነታቸው ተመልሰው መብረር ጀመሩ። ኢብራሒምም (ዐለይሂ ሰላም) ይህንን ትዕይንት እና የ አላህን ችሎታ በ አይናቸው ተመለከቱ። አላህም እኔ አሸናፊ ጥበበኛ መሆኔን እወቅ አላቸው።
ኢብራሒም በጠየቁት መሰረት ሙታንን እንዴት ህያው ማድረግ እንደሚችል በቁሳዊ መንገድ መልስ ሰጣቸው። ዳግም ህይወት የመዝራትን የመቅስቅስን ትክክለኛ ምንነት ግን አላብራራላቸውም። ምክናየቱም ህይወት መዝራት ከሰው ልጅ አዕምሮ የመረዳት አቅም በላይ ነው።
#ሩህ ተዐምራዊ ሚስጥሩን አላህ እንጅ ማንም ሊደርስበት የማይችል ድንቅ የፈጣሪ ችሎታ ናት ቁርአን እንድህ ይላል፡- á
#ከሩሕም ይጠይቁሃል። «ሩሕ ከጌታዬ ነገር ነው ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም» በላቸው።

(አል ኢስራዕ 85)
ስለ ሩህ ማንም ማወቅ እንደማይችል እንድሁም የሰው ልጅወች ያላቸው እውቀት ጥቂት እና ውስን እንደሆነ በዚህ የ ቁርአን አንቀፅ ያብራራል።
#ይ_ቀ_ጥ_ላ_ል .....
http://t.me/AshaBuleyamine

ቀጣይ ሥራዎችን
@tafachdaewachanal ይከታተሉን
@mahircomp123
@Alfurqan11
@Alfurqan12
@sunatube